# የ2ኛ ቆሮንቶስ ጥናት(36)

## ጥናት አንድ 2ኛ ቆሮ 1፡1-11

የጥናት ዓላማ፡- በእግዚአብሄር ፈቃድ ወደ እኛ ህይወት የሚመጣ መከራ ሁሉ፤ ምንጊዘም ቢሆን ህይወታችን የልጁን መልክ እንዲመስል ለመሥራት እንጂ እኛን ለማፍረስ መከራ እንደማይመጣ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹በእርግጥ የሞት ፍርድ እንደተፈረደብን ይሰማን ነበር፤ ይህም የሆነው ሙታንን በሚያስነሳ በእግዚአብሄር እንድንታመን እንጂ በራሳችን እንዳንታመን ነው፡፡›› 2ኛ ቆሮ 1፡9

1. 2ኛ ቆሮ 1፡1-11 በአንድነት ይነበብ፡፡ ስለ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስትያን ስታስብ አስቀድሞ ወደ አዕምሮህ የሚመጣው የመጀመሪያ ነገር ምንድነው? በቁ1-2 ይህችን ቤተ ክርስትያን ጳውሎስ ንብረትነቷን የማን አድርጎ ነው የሚናገረው? ይህች ርኩሰትና አመጽ ለሞላባት ቤተ ክርስትያን በዚህ አይነት ስም መጠራት ምን ያስተምረናል?
2. ቁ3 ላይ ለእግዚአብሄር መጠሪያ ሆነው የተነገሩት ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው? የርህራሄ አባት የሚለውን አነጋገር የምትረዳው እንዴት እንደሆነ ግለጽ፡፡
3. ቁ4ትን በማንበብ መጽናናትን አስመልክቶ ልንማር የምንችላቸውን ቢያንስ ሁለት እውነቶችን ተናገር፡፡ ይህ ቁጥር ጌታ የሱስን ያመነ ሰው መከራ ሊያገኘው አይችልም ወይም አይገባም ከሚለው አስተሳሰብ ጋራ የሚቃረነው በምን ዓይነት ነው? አንተ ያለፍከበት መከራ ለሌላው መጽናናት የሆነበት ሁኔታ፤ ወይም ደግሞ ሌላ ሰው ያለፈበት መከራ ለአንተ መጽናናት የሆህ ካለ ለወገኖች አካፍል፡፡
4. ከ3-7 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ጳውሎስ ያተኮረባቸው ሁለት ቃላት ምንና ምንድናቸው? ቁ6 ላይ ‹‹መከራ ብንቀበል ስለእናንተ መጽናናትና መዳን ነው›› ከሚለው አነጋገሩ ስለነጳውሎስ መከራውን አቀባበል ሁኔታ ምን ያስረዳናል? ለሌሎች መዳንና መጽናናት ስትል መከራን ለመቀበል ምን ያህል ልብህ የተዘጋጀ ነው?
5. በቁ7 ላይ ጳውሎስ በእርግጠኛነት የሚናገረው አንድ ነገር ምንድነው? ከዚህ አነጋገሩ በመከራና በመጽናናት መሃል ስላለው ግንኙነት ምን ትረዳለህ?
6. ጳውሎስና ጓደኞቹ በእስያ የደረሰባቸውን የመከራ ክብደት የሚጠቁሙ ሃሳቦችን ከ8-9 ካሉት ቁጥሮች ውስጥ በማውጣት ተናገር፡፡ እነ ጳውሎስ በእስያ ስለደረሰባቸው መከራ የቆሮንቶስ ሰዎች እንዲያውቁ የፈለገበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል?
7. ቁ10-11ድን ስናነብ እግዚአብሄር በእስያ ባደረገው ማዳን ብቻ የማይወሰን እንደሆነ የተረጋገጠው በምን መንገድ ነው? በጳውሎስ አመለካከት ከመከራ እንድንድን ቅዱሳን ያላቸው አስተዋጽዖ ምንድነው? በመከራ ውስጥ ራስህን ስታገኝ የቅዱሳን ጸሎት እንደሚያስፈልግህ፤ አንተ በምታልፍበት ሁኔታም የቅዱሳን ጸሎት ያስፈልግሃል፡፡
8. አነጳውሎስ በቁ8-11 እንደምናየው በከባድ መከራ አልፈዋል፡፡ ይህ ሁሉ መከራ የደረሰባቸው በምንባቡ መሰረት ለምንድነው? በጊዜው መልካም ከማይመስለው መከራ እግዚአብሄር መልካም ነገር ማውጣቱ ለአንተ ምን ትምህርት ይሰጥሃል? በእግዚአብሄር ፈቃድ ወደ ህይወትህ የሚመጣ ማናቸውም መከራ ሊያበጅህ እንጂ ሊያጠፋህ እንደማይመጣ ልትረዳ ይገባሃል፡፡

# ጥናት ሁለት 2ኛ ቆሮ 1፡12-24

የጥናት ዓላማ፡- በሰዎች ህይወት ለውጥ ማምጣት የምንችለው፤ ማድረግ የሚገባቸውን ዝርዝር በመንገርና በማዘዝ ሳይሆን፤ ከልባቸው ፈቅደው፣ በደስታና በመረዳት መለወጥ እንዲፈልጉ በመርዳት እንደነጳውሎስ አብሮ በመስራት እንጂ በነርሱ ላይ በመሰልጠን እንዳልሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ጸንታችሁ የምትቆሙት በእምነታችሁ ስለሆነ፣ ደስ እንዲላችሁ ከእናንተ ጋራ እንሰራለን እንጂ በእምነታችሁ ላይ ለመሰልጠን አይደለም፡፡›› 2ኛ ቆሮ 1፡24

1. 2ና ቆሮ 1፡12-24 በአንድነት ይነበብ፡፡ የቁ12-24 አጠቃላይ ሃሳብ ምን እንደሆነ በአጭሩ አስረዳ፡፡
2. ቁ12 ላይ የነጳውሎስ ትምክህት ምንድነው? ትምክህተኛነት ትክክል እንዳልሆነ 1ኛ ቆሮ 13፡4 ላይ እናነባለን፤ ታዲያ ለምንድነው በዚህ ስፍራ እነጳውሎስ የሚመኩት?
3. በ2ኛ ቆሮ 1፡13-14 እና 1ኛ ቆሮ 13፡12 ላይ የምናነባቸው ጥቅሶች እኛ የሰው ልጆች በዚህ በምድር ላይ ስንኖር ስለሚኖር ስለሚኖረንና ጌታ ደግሞ ሲመጣ እውቀትን አስመልክቶ ስለሚኖረን ለውጥ ምን ያስተምሩናል? በነዚህ ጥቅሶች መነጽር ስንመለከተው በጳውሎስና በቆሮንቶስ ቅዱሳን መሃል ችግር ያስከተለው ነገር ምንድነው? ሰዎች ያወቁህ መስሏቸው የፈረዱብህ፤ ወይም ደግሞ አንተ ሰዎችን ሙሉ ለሙሉ ያወቅሃቸው መስሎህ ፍርድ ያስተላለፍክበት ጊዜ ይኖር ይሆን ወይ?
4. በቁ15-17 መሰረት የጳውሎስ የልቡ ፍሎጎት ለቆሮንቶስ ቅዱሳን ምን እንደነበረ ነው የምናየው? እነዚህኑ ቁጥሮች በትኩረት ስናይ የቆሮንቶስ ሰዎች እቅዱን የተመለከቱበት መንገድስ ምን ይመስላል? ለሰዎች በጎን አስበህ ያደረከው ነገር በክፉ መንገድ ተተርጉሞብህ ያውቃል ወይ? ምሳሌ ካለህ ለወገኖች አካፍል፡፡
5. በቁ18 ላይ ያለው ሃሳብ በማቴ 5፡37 ላይ ኢየሱስ ከተናገረው ሃሳብ ጋራ የሚመሳሰለው በምን መንገድ ነው? በዚህ ክፍል ውስጥ እነጳውሎስ እየተከተሉ ያሉት የማንን ፈለግ ነው? አንተስ የምትከተለው የማንን ፈለግ ነው?
6. እነኚህ ሶስት ኋደኛሞች ለቆሮንቶስ ሰዎች የሰበኩላቸው ማንን ነው? በቁ19 አነጋገር ‹‹አዎን›› እና ‹‹አይደለም›› የሚሉት አነጋገሮች ምን ማለት እንደሆኑ አስረዳ፡፡
7. እግዚአብሄር በአማኞች ህይወት የሰራቸውና የሚሰራቸው በቁ21-22 ላይ የምናነባቸውን አራት ነገሮች ዘርዝር፡፡ የእነዚህ ሁሉ በረከቶች ተካፋይ ስለሆኑት ሰዎች ማንነት ከነዚህ ቁጥሮች ምን እናያለን? የእግዚአብሄር ንብረት እንደሆንክና ማህተሙ እንዳለብህ ሰው ትመላለሳለህ ወይ?
8. ቁ23-24ትን ሰታይ በአገልጋዮቹና በተገልጋዮቹ መሃል ስለነበረው ግንኙነት ምን ትረዳለህ? ሰዎች በክርስቶስ ለያገኙ ለሚችሉት ደስታ ምን ያህል ተደክማለህ? በሰዎች ህይወት ለውጥ ማምጣት የሚቻለው በንግግርና በጭቅጭቅ ብዛት ብዛት ሳይሆን እድገትን እንዲናፍቁ ለማድረግ አብሮ በመስራት እንደሆነ ልንረዳ ያስፈልጋል፡፡

# ጥናት ሶስት 2ኛ ቆሮ 2፡1-17

የጥናት ዓላማ፡- ይቅርታ ማድረግን መለማመድ ለበግል ህይወታችንም ሆነ ለቤተክርስትያን አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ፤ ይቅርታን አለማድረግ ደግሞ ለሰይጣን መግቢያ ቀዳዳን የሚሰጥ ክፉ ነገር ስለሆነ ልንጠነቀቅ እንደሚገባን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹…በክርስቶስ ፊት ይቅር የምለው ስለእናንተ ስል ነው፡፡ ይህንንም የማደርገው ሰይጣን መግቢያ ቀዳዳ እንዳያገኝ ነው፤ የእርሱን ዕቅድ አንስተውምና፡፡›› 2ኛ ቆሮ 2፡10-11

1. 2ኛ ቆሮ 2፡1-17 በአንድነት ይነበብ፡፡ ከ1-4 ባሉት ቁጥሮች ላይ የተተኮረባቸው ሁለት ቃላት ምንና ምንድናቸው? ለጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ላለመሄድ ምክንያት የሆነው ነገር ምን ነበረ?
2. ጳውሎስ ፊት ለፊት አግኝቶ የነበረውን ችግር ለመፍታት ከመሞከር ይልቅ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የመረጠው ነገር በደብዳቤ ወይም በጽሁፍ ለማድረግ እንደሆነ ከቁ3 እንረዳለን፡፡ ለምን ይመስልሃል ጳውሎስ በዚህ መንገድ መሄድ የመረጠው? 1ኛ ቆሮ 1፡24 ትንና 2፡3 ትን ሰናነብ በወንጌል አገልግሎት የሚገኘው ደስታ ተካፋይ ሊሆኑ የሚገባቸው እነማን ናቸው?
3. ደብዳቤውን ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲጽፍ ጳውሎት ስለተሰማው ስሜት ከቁ4 ምን እናነባለን? ደብዳቤው በቆሮንቶስ ሰዎች ሊፈጥር የሚችለውን ስሜት ያውቅ ነበረ ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡
4. ጳውሎስ በተለይ በቁ4 ላይ የቆሮንቶስ ሰዎች ስለደብዳቤው መንፈስ እንዲረዱለት የፈለገው አንድ ሃሳብ ምን ይመስልሃል? ከየቆሮንቶስ ሰዎች እንደሚያዝኑ እያወቀ የወሰደውን እርምጃ ከምሳሌ 27፡6 እና ከኤፌ 4፡15 ጋራ በማነጻጸር ለመናገር ሞክር፡፡ ወዳጆችህ ቢያማቸውም እንኳን እውነቱን የመናገርን ምን ያህል ትለማመዳለህ?
5. ቁ5-8 በነዚህ ቁጥሮች ላይ ቅዱሳኑ እንዲያደርጉ የሚጠየቋቸውን ቢያንስ ሶስት ነገሮች ዘርዝር፡፡ በዚህ ሰው ላይ ቅጣቱን የወሰነው ሰው ማን እንደሆነ ነው የምናነበው? ከነዚህ አራት ቁጥሮች ውስጥ የተማርከው እውነት ምን እንደሆነ ለቅዱሳን አካፍል፡፡
6. ቁ9-11 በነዚህ ቁጥሮች ላይ ጳውሎስ ይቅርታንና ሰይጣንን በምን መንገድ ነው ሲያገናኝ የምናየው? ይቅርታን ለማድረግ አሻፈረኝ ወይም እንቢ የሚል ክርስትያን በተለይ ቁ11ድን አስመልክቶ የሳተው አንድ ትልቅ ነገር ምንድነው? ይቅርታን ላለማድረግ አሻፈረኝ ብለህ ወይም ሌላ ሰው በዚህ ሁኔታ ገጥሞህ የሚያውቅ ከሆነ ስም ሳትጠቅስ ለትምህርት ያህል ተናገር፡፡
7. ቁ12-13 ትንና 7፡5-7 በአንድነት ይነበብ፡፡ ጳውሎስ የተከፈተለትን የአገልግሎት በር ላለመጠቀም የወሰነው ለምን ነበረ? ለጳውሎስ መጽናናት ምክንያት የሆኑለት ነገሮች ምን ነበሩ? ጳውሎስ ላዲሶች ወንጌል በመስበክና፤ የዳኑትን አማኞች በማነጽ መኃል ስላለው ሚዛናዊ አመለካከት ምን ታረዳለ?
8. ቁ14-17 እውነተኛ የወንጌል አገልጋይ ምን አይነት ህይወት ሊኖረው እንደሚገባው እነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የሰፈሩትን በመዘርዘር ተናገር፡፡
9. 2 ቆሮ 2፡11 እና ኤፌ 4፡27 ስናነብ ሰይጣን በአማኝ ህይወትም ሆነ፣ በቤተክርስትያን ራሱን ሊያስገባ መንገድ የሚከፍትለት ነገር ምንድነው? በራስህ ህይወትም ሆነ፣ በቤተክርስትያንህ ሰይጣን ቀዳዳ እንዳያገኝ ምን ያህል ጥንቃቄ ታደርጋለህ? ይቅርታ አለማድረግ ዋነኛው ለሰይጣን ወደ ህብረታችን ለመግባት የሚያስችለው የመግቢያ በር ስለሆነ፤ ዘወትር በርህን ዘግተህ ማቆየትህን አትዘንጋ፡፡

# ጥናት አራት 2ኛ ቆሮ 3፡1-18

የጥናት ዓላማ፡- እኛ የአዲስ ኪዳን አገልጋዮች ባልተሸፈነ ፊት የጌታን ክብር የምንገልጥ ብቻ ሳንሆን፤ ጌታ ራሱ ደግሞ የእርሱን መልክ እንድንመስል እለት በእለት ከክብር ወደ ክብር እንደሚለውጠን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እኛም ሁላችን ባልተሸፈነ ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያንጸባረቅን የእርሱን መልክ እንድንመስል ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን፤ ይህም የሚሆነው መንፈስ ከሆነ ጌታ ነው፡፡›› 2ኛ ቆሮ 3፡18

1. 2ኛ ቆሮ 3፡1-18 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-3 ላይ የቆሮንቶስ አማኞችን በምን ዓይነት ነው ለነጳውሎስ የመከላከያ መንገድ ሆነው የተጠቀሱት? በተለይ በቁ3 ላይ የተነገረው ‹‹…የተገለጣችሁ የክርስቶስ ግልጽ ደብዳቤ ናችሁ›› የሚለው አነጋገር ለአማኝ ሁሉ የሚሰራው እንዴት እንደሆነ አስረዳ፡፡
2. በ2ኛ ቆሮ 2፡16 ላይ ጳውሎስ የጠየቀው ጥያቄ በ3፡5 ላይ እንዴት ነው መልስ ሲያገኝ የምናየው? ዘካ 4፡6 ላይ የተነገረው ሃሳብ በዚህ ቁጥር ላይ ከሰፈረው ሃሳብ ጋራ በማነጻጸር አገልግሎትን አስመልክቶ መማር የምንችለው አንድ እውነት ተናገር፡፡
3. በቁ6 ላይ ስንመለከት በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን መሃል ስላለው ልዩነት ምን ይነግረናል? በዚህ ክፍል አነጋገር መሰረት ‹‹ፊደል›› እና ‹‹መንፈስ›› የሚሉትን ሁለት ቃላት ሃዋርያው የተጠቀመባቸው ምንን ለመግለጥ ነው ብለህ ታምናለህ? ለወንጌል አገልግሎት እግዚአብሄር ብቃትን እንደሰጠህ ምን ያህል አምነህ ተቀብለሃል?
4. ቁ7-11ድን ስታነብ የብሉይ ኪዳንን አገልግሎትን ለመግለጥ የተጠቀመባቸውን ጥቂቶቹን ሃሳቦች በመዘርዘር ተናገር፡፡ በዚሁ አንጻር የአዲስ ኪዳኑን አገልግሎትስ ለመግለጥ የተጠቀመባቸውን አንዳንዶቹን ሃሳቦች ተናገር፡፡
5. በአንተ አመለካከት በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በተለይ የብሉይ ኪዳንን አገልግሎትን አስመልክቶ የተነገሩትን ሃሳቦች ስታይ፤ ጳውሎስ የብሉይ ኪዳን መሰጠት አስፈላጊ አልነበረም፤ ወይም ደግሞ ብሉይ ኪዳን ምንም ጥቅም የለውም ለማለት ፈልጎ ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡
6. በቁ12-13 አነጋገር መሰረት የአዲስ ኪዳን አገልጋዮች በሙሉ ልብና በድፍረት ሊናገሩ የሚያስችላቸው ነገር ምንድነው? ጳውሎስ ተስፋ በማለት በዚህ ክፍል የሚናገረው ስለየትኛው ነገር ነው? ይህ ተስፋ ለአገልግሎትህ ድፍረትና መነቃቃት ሆኖልህ ያውቃል ወይ?
7. ቁ14-17ትንና 2ኛ ቆሮ 4፡3-6 በአንድነት በማንበብ መሸፈኛው ስለሚወገድበት መንገድና ሰዎች ወደ እምነት ሊመጡ ስለሚችሉበት ሁኔታ እነዚህን ሁለት ክፍሎች ጎን ለጎን በማንበብ ልንደርስበት የምንችለው አንድ እውነት ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
8. በቁ18 ላይ የእኛ አገልግሎት ከሙሴ ስለሚለይበት ሁኔታ የሚነግረን ነገር ምን ምን ነገሮች እንደሆኑ ተናገር፡፡ ህይወትህ የኢየሱስን መልክ እንዲመስል ከክብር ወደ ክብር እየተለወጠ ነው ወይ? የጌታን ክብር የምትገልጥ ብቻ ሳትሆን፤ አንተም ራስህ ደግሞ ከክብር ወደ ክብር የምትለወጥ አገልጋይ መሆንህን አትዘንጋ፡፡

<u>ጥናት አምስት 2ኛ ቆሮ 4:1-18</u>

የጥናት ዓላማ፡- ማንኛችንም ብንሆን የውጫዊውን ሰውነታችንን መበስበስና ማርጀት ማቆም ወይም መለወጥ እንደማንችል የታወቀ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ግን ሁላችንም የውስጣዊው ሰውነታችን እለት በእለት መታደስና አለመታደስ ሁኔታ እኛ ራሳችን እንደሆንን እንድንረዳ ለማድረግ፡፡ የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ስለዚህ ተስፋ አንቆርጥም፤ ውጫዊው ሰውነታችን እየጠፋ ቢሄድም እንኳን፣ ውስጣዊ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል፡፡›› 2ኛ ቆሮ 4፡16

1. 2ኛ ቆሮ 4፡1-18 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-2 ላይ ጳውሎስ ‹‹ይህ አገልግሎት›› እያለ የሚናገረው የትኛውን አገልግሎት ነው? ይህንን አገልግሎት የተቀበለ ሰው ማድረግ ስላለበትና ስለሌለበት ነገሮች እነዚህ ቁጥሮች ምን ይነግሩናል?
2. ጳውሎስ በቁ2 ላይ ‹‹እውነትን በግልጽ እየተናገርን በሰው ሁሉ ህሊና ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረን ራሳችንን በእግዚአብሄር ፊት እናቀርባለን፡፡›› ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ አስረዳ፡፡
3. በቁ3-6 መሰረት የወንጌል መልዕክት እንደተከደነባቸው አድርጎ ሚናገራቸው ሁለት አይነት ሰዎች ምናና ምን በማለት ነው የሚጠራቸው? እነዚህ ሁለቱ ዓይነት ሰዎች የተለያዩ ናቸው ብለህ ታምናለህ ወይ?
4. በቁ4 ላይ የዚህ ዓለም ገዢ በመባል የታወቀው ሰይጣን የሚሰራውን ሥራና፤ በቁ6 ላይ ደግሞ እግዚአብሄር የሚሰራውን ስራ በማነጻጸር ተናገር፡፡ እግዚአብሄር በሰዎች ልብ ብርሃኑን እንዲያበራ  የወንጌል አገልጋይ ተሳትፎው ምንድነው ትላለህ? አንተስ በዚህ ሥራ ውስጥ ተሳትፎ ታሳያለህ ወይ?
5. ለወንጌልን በቁ7 ላይ የተሰጠው ሁለት ስሞች ምንና ምንድናቸው? እንደዚህ አይነቱን ነገር እግዚአብሄር በምን ውስጥ ነው ያስቀመጠው? ይህ ድርጊቱ በቁ1 ላይ ጳውሎስ የተናገረውን እውነት እንዴት እንደሚያረጋግጥልን አስረዳ፡፡
6. የወንጌል አገልጋይ ቁ7-12 በሰፈሩት ነገሮች ውስጥ በማለፉ የሚጠቀሙት ሶስት ዓይነት ሰዎች እነማን መሆናቸውን ከቁ13-15 አውጥተህ በመናገር፤ በተጨማሪም  የያንዳንዱ ጥቅም ምን እንደሆነ ጨምረህ አብራራ፡፡
7. ቁ16-18 ላይ ዛሬ እኛ የምናልፍባቸውን መከራችንን ምን በማለት ነው ከሚያስገኝልን ነገር ጋራ የሚያነጻጽረው? በተለይም በቁ18 ላይ የሚታይና የማይታይ ብሎ የሚናገረው ምኑን ነው? አይንህ በጊዜያዊና ዛሬ በምታየው በመከራህ ላይ ነው ወይስ ዛሬ በማታየውና ዘላለማዊ በሆነው ክብር ላይ?
8. በነዚህ ቁጥሮች በተለይም ቁ16 ላይ የሚያነጻጽራቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? በአንተ አመለካከት በውጫዊው ሰውነታችን ከሚካሄደውና በውስጥ ሰውነታችን ይካሄዳል በማለት ሃዋርያው ከሚናገራቸው ነገሮች እኛ ልንቆጣጠረው የምንችለው የትኛውን ነው ብለህ ታምናለህ? የውስጥ ሰውነትህ እለት እለት ይታደሳል ወይ? የውጫዊ ሰውነትህን እርጅና ማቆም ባትችልም፤ የውስጡን ሰውነትህን ግን እድገትና እለት በእለት የመታደስ ሁኔታ በአንተ እጅ እንደሆነ መዘንጋት የለብህም፡፡

# ጥናት ስድስት 2ኛ ቆሮ 5፡1-10

የጥናት ዓላማ፡- ደህንነታችን በክርስቶስ የተፈጸመና ያለቀ ነገር ቢሆንም፣ እንደ ክርስትያን በምድር በምንመላለስበት ዘመናችን ላደረግናቸው በጎም ሆኑ ክፉ ሥራዎቻችን አንድ ቀን በጌታ በየሱስ የፍርድ ዙፋን ፊት መቆማችን እንደማይቀር ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንቀርባለንና፤ እያንዳንዱም ሰው በስጋው ለሰራው በጎ ወይም ክፉ ስራ ተገቢውን ዋጋ ይቀበላል፡፡›› 2ኛ ቆሮ 5፡10

1. 2ኛ ቆሮ 5፡1-10 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-4 ላይ ሃዋርያው እያነጻጸረ የሚናገራቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ስለ እነዚህ ሁለት ነገሮች ይህ ክፍል በማረጋገጥ የሚነግረን ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ  በመዘርዘር ተናገር፡፡
2. እነዚህን ቁጥሮች ስንመለከት መቼ ነው ሰማያዊ መኖሪያችንን የምንለብሰው? ‹‹ሰማያዊ መኖሪያ›› ሲል ምን ማለቱ ነው? ምድራዊው መኖሪያችን እስከሚፈርስበት ጊዜ ድረስ ስለምናደርገው ነገር እነዚህ ሁለት ቁጥሮች ምን ይነግሩናል? የሰማዩን ሰውነት ለመልበስ ትናፍቃለህ ወይስ ይህ ፈራሹ ያጓጓሃል?
3. ‹‹ምድራዊ ድንኳን›› እያለ በዚህ ክፍል የሚናገረው ይህችን የምንኖርባትን ምድር ማለቱ ነው ወይስ ይህንን ምድራዊ አካላችንን ነው? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡ ቁ3-4 ያለው ሃሳብ ምን ሊል እንደፈለገ በራስህ አነጋገር አስረዳ፡፡
4. ቁ5 ‹‹ለዚህ ዓላማ›› በመባል የተነገረለት የትኛው አላማ ነው ብለህ ታምናለህ?
5. ቁ6-8ትን ስናነብ ሐዋርያው ህይወቱን የሚኖረው በምን መንገድ ነው? ለምን ይመስልሃል ይህ ሊሆን የቻለው? የአንተስ ኑሮ በእምነት ነው ወይስ በማየት?
6. እነዚህን ሶስት ቁጥሮች ስታነብ አማኝ ሊገኝ የሚችልባቸው ሁለቱ አማራጮች ምንና ምንድናቸው? ፊሊ 1፡23ትን ስታይ የጳውሎስ ምርጫ ከዚህ አንጻር ምን ነበረ? ዛሬ በምናጠናው ክፍል አነጋገር ጳውሎስ የአማኝ ሁሉ ምርጫ ይሆናል ብሎ የሚያስበው አመለካከትስ የትኛው ነው?
7. በቁ9-10 ላይ ለጳውሎስ በስጋ መሆንና ከሥጋ መለየት ለእርሱ የሚያመጡት ምንም ዓይነት ልዩነት እንደሌለ አድርጎ የሚናገረው ከምን አንጻር እያየው ነው? ‹‹ዓላማችን›› እና ‹‹ሁላችን›› እያለ የሚናገረው ስለማን ነው? ለምን ይህንን ለማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡
8. ቁ10 የሚናገረው ከደህንነት ጋራ እንደማይገናኝ በምን መንገድ ነው ኤፌ 2፡8-9 ግልጽ የሚያደርግልን? ቁ9ኝን ለህይወቱ መመሪያ በማድረግ ለሚመላለስ ሰው ቁ10 ያስፈራዋል ብለህ ታምናለህ ወይ? በምድር  ስትኖር ለእያንዳንዱ ድርጊትህ በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት መልስ እንደምትሰጥበት እያሰብክ ትኖራለህ ወይ? መልካም ሆነ ክፉ ለምታደርገው ሁሉ ለጌታ መልስ የምትሰጥበት ስለሆነ በማስተዋል ልትመላለስ እንደሚገባህ አትዘንጋ፡፡

# ጥናት ሰባት 2ኛ ቆሮ 5፡11-21

የጥናት ዓላማ፡- እንደ ክርስቶስ እንደራሴ ዋነኛና የመጀመሪያው ተልኮአችን ሰዎችን ሁሉ ከእግዚአብሄር ጋራ ታረቁ የሚለውን መልዕክት እንዲሰሙ በምንችለው መንገድ ሁሉ ማስተጋባት እንደሆነ መዘንጋት እንደለለብን ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ስለዚህ እኛ የክርስቶስ እንደራሴዎች ነን፤ እግዚአብሄርም በእኛ አማካኝነት ጥሪውን ያቀርባል፤ እኛም ከእግዚአብሄር ጋራ ታረቁ ብለን በክርስቶስ እንለምናችኋለን፡፡›› 2ኛ ቆሮ 5፡20

1. 2ኛ ቆሮ 5፡11-21 በአንድነት ይነበብ፡፡ ጳውሎስ በቁ11 ላይ የሚናገረው ‹‹ጌታን መፍራት›› ከምን ጋራ የተያያዘ ነው? ከላይ በቁ10 ላይ የተነገረው የፍርድ ወንበር ጉዳይ በግድ የለሽነት መታየት የሌለበት ነገር መሆኑን ከጳውሎስ አነጋገርና ድርጊት መረዳት የምንችለው እንዴት ነው?
2. ቁ11-12ት ሲነበብ በተለይም ቁ11 ላይ የእነጳውሎስ ማንነት በእግዚአብሄርና በቆሮንቶስ ሰዎች ዘንድ እንዴት ነው የሚታዩት? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እነጳውሎስ ስለማንነታቸው መናገር ያስፈለገበት ምክንያት ለምንድነው ብለህ ታምናለህ?
3. ማር 3፡21 ፤ ሐዋ ሥራ 26፡24 እና 2ኛ ቆሮ 5፡13 ትን ስናነብ ጳውሎስና ኢየሱስ የሚመሳሰሉበት አንድ ነገር ምንድነው? እብድነታቸው ለእግዚአብሄር፤ ባለአዕምሮነታቸው ደግሞ ለተገልጋዮቹ እንደሆነ ጳውሎስ ይናገራል፤ ይህንን ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ አስረዳ፡፡ አንተስ ለክርስቶስ እንደእብድ የተቆጠርክበት ጊዜ ገጥሞህ ያውቃል ወይ?
4. ቁ14-15 ‹‹ከዚህም የተነሳ ሁሉ ሞተዋል፡፡ በህይወት ያሉትም…›› ሁሉም ከሞቱ እንዴት ነው ይህ ክፍል በህይወት ስላሉት ሊያወራ የሚችለው? በዚህ ክፍል አነጋገር መሰረት የኢየሱስ ክርስቶስ ለሁሉ በመሞቱ ምክንያት በእርሱ ባመኑት ሰዎች ህይወት ውስጥ መከሰት ያለበት አንድ እውነት ምንድነው ምንድነው? አንተስ ዛሬ ህይወትህን የምትኖረው ለማን ነው?
5. ቁ16 ላይ ‹‹ስለዚህ ከአሁን ጀምሮ›› የሚለው አነጋገር የሚጠቁመን ወደየትኛው ጊዜ ነው? በቁ15 ላይ በህይወት ያሉት ለሞተላቸው እንጂ ለራሳቸው ያለመኖራቸውነገር፤ በቁ16 ላይ  በህይወታቸው ሲገለጥ የምናየው በምን መንገድ ነው?
6. ቁ17-18 ‹‹ማንም በክርስቶስ ቢሆን›› የሚለውን ሃሳብ ከዮሐ 15፡4 ጋራ በአንድነት በማንበብ በማንበብ ምን ማለት እንደሆነ አስረዳ፡፡ በነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ ‹‹ይህ ሁሉ ከእግዚአብሄር ነው›› የሚለው ምን ነገሮች ሊሆኑ እንደሚችሉ የምታየውን ሁሉ በመዘርዘር ተናገር፡፡
7. በቁ18-21 ላይ ዋነኛውን ሥፍራ የያዘው አንድ ቃል ምንድነው? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ከእግዚአብሄር ጋራ የታረቁ ሰዎችን አስመልክቶ የተነገሩት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
8. የአንድ አገር እንደራሴ ሆኖ ወደሌላ ሀገር የተላከ ሰው እንዲሰራ የሚጠበቅበት ነገሮች ተናገር፡፡ በቁ18-21 ስታይ የእግዚአብሄር አምባሳደር ((እንደራሴ) የሆነ ሰው ዋነኛው ተልዕኮ ምን እንደሆነ ነው የሚገባህ? አንተስ ሰዎችን ከእግዚአብሄር ጋራ ታረቁ የሚለውን መልዕክት እያስተጋባህ ነው ወይ? እንደ ክርስቶስ እንደራሴ ዋናና የመጀመሪያው ተልዕኮህ ከእግዚአብሄር ጋራ ታረቁ የሚለውን መልዕክት ሰዎች ሁሉ እንዲሰሙ ማድረግ ስለሆነ ትኩረት ልትሰጠው የሚገባህ ነገር መሆኑን አትዘንጋ፡፡

# ጥናት ስምንት 2ኛ ቆሮ 6፡1-18

የጥናት ዓላማ፡- የእግዚአብሄር ቤተመቅደስ በመሆን የሚገኙትን ጥቅሞች ላይ ብቻ በማተኮር፤ ከጥቅሞቹ ጋራ የሚመጡትንም ሃላፊነቶች ሁሉ ተረድተን በህይወታችን ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹የእግዚአብሄር ቤተመቅደስ ከጣዖታት ጋር ምን ስምምነት አለው? እኛኮ የህያው እግዚአብሄር ቤተመቅደስ ነን…ስለዚህ ከመካከላቸው ውጡ፣ ለእኔም የተለያችሁ ሁኑ፣ ይላል ጌታ›› 2ኛ ቆሮ 6፡16-17

1. 2ኛ ቆሮ 6፡1-18 በአንድነት ይነበብ፡፡ አማኞችን በቁ1-2 ውስጥ በምን መልኩ ነው የሚያስተዋውቃቸው? ‹‹ከእግዚአብሄር ጋራ አብረን የምንሰራ…›› ብሎ ሲናገር ከእግዚአብሄር ጋራ የምንሰራው ስራ ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
2. በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ ‹‹የተቀበላችሁት የእግዚአብሄር ጸጋ›› በማለት የሚናገረው ነገር ስለየትኛው ጸጋ ነው? በቁ2 ላይ ከኢሳይያስ 49፡8 በመጥቀስ የተናገረው ነገር ከዚህ ጸጋን ስለመቀበል ከተናገረው ነገር ጋራ እንዴት ነው ሊገናኝ የሚችለው? የተሰጠህ የማስታረቅ አገልግሎት ነገ የሚያሰኝና ቀጠሮ የማያሰጥ መሆኑ ምን ያህል ገብቶሃል?
3. በቁ3 ላይ ሐዋርያው በህይወቱ ውሳኔ ያደረገበትና ሰዎች ሁሉ እንዲያውቁለት የሚፈልገው አንድ እውነት ምንድነው? በ2ኛ ቆሮ 6፡3 እና በ1ኛ ቆሮ 8፡9 መካከል የምታያቸውን መመሳሰልም ሆነ ልዩነቶች ሁሉ በመዘርዘር ተናገር፡፡
4. ቁ4-10 ላይ ለጳውሎስና ከእርሱ ጋራ ለነበሩት ራሳቸውን እንደ እግዚአብሄር አገልጋዮች በማቅረባቸው ምክንያት በህይወታቸው ያሳለፏቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? እኛስ እንደ እውነተኛ የእግዚአብሄር አገልጋዮች መመላለሳችን እነዚህን ሁሉ እንደሚያስከትልብን ብናውቅ ፈቃደኛ እንሆናለን ወይ?
5. በቁ10 ላይ ‹‹ድሆች ስንሆን ብዙዎችን ባለጠጎች እናደርጋለን›› የሚለው አነጋገር ምን ማለት እንደሆነ አስረዳ፡፡ በተጨማሪም ደግም ‹‹ምንም የሌለን ስንሆን ሁሉ የእኛ ነው፡፡›› ሲል ምን ለማለት ፈልጎ እንደሆነ ተናገር፡፡
6. በቁ11-12 ውስጥ ጳውሎስና ጓደኞቹ ለቆሮንቶስ ሰዎች ያላቸውን ስሜት ስለገለጡባቸው መንገዶች የሚታዩትን ሶስት ነገሮች ዘርዝር፡፡ እነዚህ ሰዎች ከቆሮንቶስ አማኞች የሚፈልጉት ነገር ምንድነው? እነዚህ ሁለት ቁጥሮች ስለነዚህ አገልጋዮች ለሚያገለግሏቸው ሰዎች ስላላቸው ልብና ስሜት ምን ያስረዳሃል? የእኛ ችግር ዛሬ ይህንን ይመስላል ወይ? በዚህ ሃሳብ ላይ ተወያዩበት፡፡
7. ቁ14-16ትን ስንመለከት ሐዋርያው የቆሮንቶስን አማኞች የሚያስጠነቅቃቸው አንድ ነገር ምንድነው? ‹‹ከማያምኑ ሰዎች ጋራ አግባብ ባልሆነ መንገድ አትጠመዱ›› ለሚለው አነጋገር ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉትን ነገሮች በመዘርዘር ተወያዩባቸው፡፡ ይህንን አነጋገር ለማነጻጸር የተጠቀመባቸውን አምስት ሃሳቦች ተናገር፡፡
8. በ1ኛ ቆሮ 6፡19 ላይ በምናነበው ቤተመቅደስና በዚህ ምንባብ ውስጥ በቁ 16 ላይ በምናነበው መሃል ልዩነት ታያለህ ወይ? አስረዳ
9. የእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ በመሆናችን የምናገኛቸው ጥቅሞች ምንድናቸው፣ ቤተመቅደስ ከመሆናችን ጋራ አብረው የሚመጡትስ ሃላፊነቶች ምንድናቸው? የቤተመቅደስን ጥቅም ብቻ ሳይሆን አብሮ የሚመጣውንም ሃላፊነት ጠንቅቀን አውቀን ልንቀበለውና ልንኖርበት እንደሚገባን መዘንጋት የለብንም፡፡

በወንድሙ ሃብተወልድ ተዘጋጀ (253) 653-4707 ethiowengel.com

# ጥናት ዘጠኝ 2ኛ ቆሮ 7፡1-16

የጥናት ዓላማ፡- እነጳውሎስ ከሚታየው ችግር አስቀድመው በመሃላቸው የተበላሸውን ግንኙነት በማደስ ላይ እንዳተኮሩ፤ እኛም ችግሮችን ለመፍታት ከመሞከራችን በፊት ግንኙነትን ማደስ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ነገር እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እንግዲህ እኔ የጻፍኩላችሁ ስለበደለው ወይም ስለተበደለው ሰው አይደለም፤ ነገር ግን ለእኛ ምን ያህል ታማኞች እንደሆናችሁ፣ በእግዚአብሄር ፊት ራሳችሁን እንድታዩ በማለት ነው፡፡›› 2ኛ ቆሮ 7፡12-13

1. 2ኛ ቆሮ 7፡1-16 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1 ላይ አማኞች ሁሉ ራሳቸውን ለማንጻት ማበረታቻ እንዲሆን የተነገረው ነገር ምንድነው? ይህ የተስፋ ቃል በማለት ጳውሎስ የሚናገርለት ስለየትናው የተስፋ ቃል ነው? ሌላው በዚሁ ቁጥር ውስጥ ቅድስናን ለመለማመድና በቅድስና ለማደግ ምክንያት እንዲሆነን የተነገረው ሃሳብ ምንድነው?
2. ቁ2ትንና 2ኛ ቆሮ 6፡13 የመሳሰሉትን ሃሳቦች ስናነብ ሐዋርያው ከቆሮንቶስ ሰዎች እየፈለገ ያለውና እነርሱ ግን እስከዚያን ሰዓት ድረስ እንዳልሰጡት አርጎ የሚያምነው ነገር ምንድነው? ለምን ይመስልሃል በቁ2 ላይ ‹‹እኛ ማንንም አልበደልንም፣ ማንንም ወደ ብልሹነት አልመራንም፣ ማንንም አላታለልንም›› እያለ የሚናገረው?
3. በቁ3-4 ላይ የቆሮንቶስ አማኞች በእነጳውሎስ ልብ ውስጥ ትልቅ ሥፍራ እንዳላቸው ለማረጋገጥ ጳውሎስ የተጠቀመበት ጠንካራ አነጋገር ምን የሚል ነው? ‹‹በመከራችንም ሁሉ ደስታዬ ወሰን የለውም›› የሚለው አነጋገር ከመጽሃፍ ቅዱስ የሚያስታውስህ የትኛውን ጥቅስ ነው?
4. ቁ5-7 ላይ እግዚአብሄር የተጠራበት አንድ ባህርይ ምን ነበረ? በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሄር አዝነው የነበሩትን እነጳውሎስን ለማጽናናት የተጠቀመባቸው መንገዶች ምንድናቸው? ሌሎች እግዚአብሄር ሰዎችን ለማጽናናት ጌታ የሚጠቀምባቸውን ልዩ ልዩ መንገዶች በማንሳት ተወያዩባቸው፡፡ እንደነጳውሎስ አንተስ በሰዎች መጽናናት ልብህ ይጽናናል ወይ?
5. በቁ7 ላይ የምናየው የጳውሎስ የደስታው ምንጭ ምን ነበረ? በቁ 7 ላይ ጳውሎስን ደስ ያሰኘው የሐዘን ዓይነት በቁ8-11 ውስጥ ምን በመባል ነው የተጠቀሰው?
6. ‹‹እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ የሆነ ሀዘን›› ለሚለው አነጋገር በ8-11 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ያሉትን በማንበብ ምን ማለት እንደሆነ የተረዳኸውን ተናገር፡፡ የዚህ ዓይነቱ ሃዘን የሚያስገኛቸው ነገሮችስ ምንድናቸው? የዚህ አይነቱ ሃዘን ተቃራኑ የሆነው ሃዘን ምን ይመስላል? እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ የሆነ ሃዘን አዝነህ ታውቃለህ ወይ? ሰዎችንስ የዚህ አይነት ሃዘን አሳዝነህ ታውቃለህ ወይ?
7. በቁ4፣ 7፣ 9፣ 13፣ 16 ስናይ ጳውሎስ በአብዛኛው ሲታይ በቆሮንቶስ ሰዎች ደስተኛ እንደነበረ ማንበብ እንችላለን፡፡ ጠቅላላ ምዕራፍ አራትን ስንቃኝ ለጳውሎስ ደስታ አስተዋጽዖ አላቸው የምትላቸውን ነገሮች ሁሉ በመዘርዘር ተናገር፡፡
8. በቁ12-13 መለስ ብለን ስናነብ ለጳውሎስ በበዳዩና በተበዳዩ ላይ ከማተኮር ይልቅ የበለጠ ትኩረት የሰጠው ነገር ምን ሆኖ ነው የምናየው? ይህ ማለት በዳይና በተበዳይ መሃል ያለውን ነገር ማስተካከል አያስፈልግም ማለት ነው ወይ? በአማኞች መሃል ሊኖር ለሚገባው የልብ አንድነት ምን ያህል ሥፍራ ነው የምትሰጠው? በቤተክርስትያን ውስጥ ችግርን መፍታት አስፈላጊ ነገር እንደሆነ ቢታወቅም፤ ነገር ግን የቅዱሳን የልብ አንድነት ከዚያ በላይ ቅድሚያ ልንሰጠው የሚገባ እውነት እንደሆነ ልንረዳ ያስፈልገናል፡፡

# ጥናት አስር 2ኛ ቆሮ 8:1-24

የጥናት ዓላማ፡- ከእግዚአብሄር ህዝብ የሚሰበሰብ ማናቸውም ዓይነት ገንዘብ በእግዚአብሄር ፊት ብቻ ሳይሆን በሰውም ፊት ነቀፋ እንደማይኖርበት ተደርጎ በብዙ ጥንቃቄና ፍርሃት ሊያዝ እንደሚገባው ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹በዚህ በምናከናውነው የቸርነት ሥራ አንዳች ነቀፋ እንዳይገኝ እንጠነቀቃለን፡፡ ምክንያቱም ዓላማችን በጌታ ፊት ብቻ ሳይሆን በሰውም ፊት መልካም የሆነውን ነገር ማድረግ ነው፡፡›› 2ኛ ቆሮ 8:20-21

1. 2ኛ ቆሮ 8:1-24 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-5 ስናነብ ጳውሎስ ስለመቄዶንያ ክርስትያኖች እንዲያውቁት የፈለገው ነገር ምን ነበረ? ይህ የተሰጣቸው ጸጋ በህይወታቸው ያስከተለውን ለውጦች ተናገር፡፡
2. በቁ5 ላይ ‹‹በመጀመሪያ ራሳቸውን ለጌታ ሰጡ፤ ቀጥለውም…ራሳቸውን ለእኛ ሰጡ›› በክርስትና ውስጥ ስለሚደረግ መስጠት ስንነጋገር ይህ አነጋገር ትልቅ ሥፍራ ሊሰጠው የሚገባው ለምንድነው ትላለህ? አንተስ ለጌታ ገንዘብም ሆነ ጊዜህን ከመስጠትህ በፊት ራስህ ልትሰጥ እንደሚያስፈልግህ ገብቶሃል ወይ?
3. ቁ6-7 ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎች ልቀው እንደተገኙ የሚነግራቸው ነገሮች ምንድናቸው? ከዚህ ጋራ በማያያዝ እነዚህ ሰዎች ምን እንዲያደርጉ ነው የሚያበረታታቸው?
4. በቁ8-9 ላይ የልግስናቸውን መጠን እንዲለኩ ወይም እንዲያስተያዩ የሚያቀርብላቸው ሁለት ምሳሌዎች ማንና ማን ናቸው? በምን መንገድ ይመስልሃል መስጠት የፍቅር ጥልቀትና እውነተኛነትን ሊያመለክት የሚችለው? የኢየሱስ ድርጊት ይህንን እውነት እንዴት ያረጋግጣል? አንተስ ፍቅርህን በመስጠት ለክተህ ታውቃለህ ወይ?
5. ቁ10-12ትን ስናነብ ጳውሎስ አንድ ፍርሃት እንዳለው እንመለከታለን፤ ይህ ፍርሃቱ ምንድነው ብለህ ታምናለህ? በዚህ ክፍል አነጋገር ስጦታን ተቀባይነት እንዲኖረው የሚያደርገው ነገር ምንድነው? ስለ ስጦታችን መጠንስ ከዚህ ክፍል ምን መማር እንችላለን?
6. በ13-15 ላይ የምናነበው ሃሳብ በተለይ ‹‹በተራው›› የሚለው አነጋገር የሚጠቁመን አንደ ሃሳብ ምንድነው? ሮሜ 15:26-27 ያለውን ሃሳብ ከዚህ ጋራ አብረን ማየት የምንችልበትን መንገድ አስረዳ፡፡
7. በቁ16-24 ውስጥ ጳውሎስ የተሰበሰበውን ገንዘብ እንዲወስዱ የተመረጡት ሰዎች እነማን ናቸው? ይህ ክፍል ስጦታው የሚሰበሰብበትንና ሁለት ምክንያቶች ሲናገር ምንና ምንድናቸው ይላል? አንተስ ማናቸውንም ዓይነት ስጦታ ስትሰጥ እነዚህን ሁለት ነገሮች አላማ አድርገህ ነው ወይ?
8. ቁ23 ላይ ሁለት ጊዜ ‹‹ስለ ቲቶ የሚጠይቅ›› ‹‹ስለ ወንድሞቻችን የሚጠይቅ›› ከሚሉት የጳውሎስ አነጋገሮች፤ ስጦታችንን የሚያስተዳድሩትን ሰዎች አስመልክቶ አንድ ልንማር የምንችለው መንፈሳዊ እውነት ምንድነው?
9. ገንዘቡን ለመውሰድ የተላኩት ሰዎች ባህርይ ምን እንደሚመስል እያንዳንዳቸውን እያነሳህ ተናገር፡፡ መልዕክተኞቹ በመልካም የተመሰከረላቸው ሆነው ሳሉ አንድ ሰው ብቻ ለለመላክ እነጳውሎስ ስለወሰኑበት ምክንያት የሚነግረን የትኛው ጥቅስ ነው ብለህ ታምናለህ? ከዚህ አድራጎታቸው ምን መማር እንችላለን? ምንም ታማኝ ቢሆን አንድን ሰው ለብቻ በገንዘብ ላይ መሾምና ሃላፊነት ማሸከም ሰውየውን ራሱን ለፈተና ማጋለጥ ሲሆን በተጨማሪም በሌሎች አዕምሮ ውስጥ ጥያቄንና ሃሜትን ሊያስከትል ስለሚችል እነጳውሎስ የወሰዱትን አይነት ጥንቃቄ መውሰድ ይጠቅማል፡፡

# ጥናት አስራ አንድ 2ኛ ቆሮ 9፡1-15

የጥናት ዓላማ፡- ልግስና የቅዱሳንን ጉድለት የሚሞላ ነገር ብቻ ሳይሆን እግዚአብሄር የሚከብርበት አገልግሎት ስለሆነ፤ በዚህ አይነት አገልግሎት መሳተፍ እንድንችል ለብዙዎቻችን ጸጋውን እንዲያበዛልን መጸለይ እንደሚኖርብን ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ይህ የምትሰጡት አገልግሎት የቅዱሳንን ጉድለት የሚያሟላ ብቻ ሳይሆን፤ ብዙ ምስጋን ለእግዚአብሄር የሚቀርብበት ነው፡፡›› 2ኛ ቆሮ 9፡12

1. 2ኛ ቆሮ 9፡1-15 በአንድነት ይነበብ፡፡ ጳውሎስ በቁ2 ላይ በአካይያ ስላሉት ሰዎች ለመቄዶንያ ሰዎች የተናገረው ነገር ምን ነበረ? በ2ኛ ቆሮ 8፡1 ላይ በአካይያ ላሉት የቆሮንቶስ ሰዎች ስለ መቄዶንያ ሰዎች የሚናገረው ነገርስ ምን ነበረ? ለምንድነው ለአንዱ ስለሌላው የሚናገርበት ምክንያት? አንተስ ሰዎችን ለማነሳሳት የሌሎችን በጎ ትናገራለህ ወይስ በሰዎች ድክመትና ውድቀት ላይ ታተኩራለህ?
2. ቁ3 ሐዋርያው በ2ኛ ቆሮ 8፡16-24 ላይ የተመለከትናቸውን ሰዎች ስለላከበት ምክንያት ምንድነው የሚላቸው? ሰዎች ለጌታ የገቡትን ቃል መፈጸም እንዲችሉ መርዳትን አስመልክቶ ከዚህ ክፍል ምን መማር እንቻላለን?
3. ከቁ4-5 አነጋገር ወደ ቆሮንቶስ ሊደረጉ የታሰቡ ስንት ጉዞዎች ታያለህ? በእነዚህ ጉዞዎች ላይ በመሪነት የምታቸው ሰዎች እነማን ናቸው? በጉዞዎቹ ላይ ተሳታፊ ይሆናሉ የምትላቸውን ሰዎች ሁሉ ለመዘርዘር ሞክር፡፡ ገንዘብ ለቅዱሳን ሰብስቦ ሰመውሰድ ምን ያህል የሰው ጉልበትና ጥራት ያላቸው ሰዎች መጠየቁ አይገርምም፡፡
4. ሐዋርያው በቁ6 ላይ ሊያስታውሳቸው የሚሞክረው አንድ እውነት ምንድነው? ይህ መርሆ ከምን የተወሰደ ነው? ይህ ጥቅስ በገላ 6፡7-8 ጋራ የሚለይበትን መንገድ ተናገር፡፡
5. በቁ7 ላይ ስንት ዓይነት የመስጠት አይነቶችን ትመለከታለህ? ከእነዚህ የመስጠት ዓይነቶች ልንከተለው ስለሚገባን የመስጠት ዓይነት ምን ይነግረናል? ለዚህስ ምክንያት ሆኖ የተነገረን ነገር ምንድነው? ‹‹በልቡ ያሰበውን ያህል ይስጥ›› የሚለው አነጋገር በውስጡ ደስታንም ያዘለ እንደሆነ መረዳት የሚያስችለህ ሃሳብ የቱ ነው? አሰጣጥህን ስትመለከተው በየትኛው ክፍል ውስጥ ትመድበዋለህ?
6. ቁ8-10ትን በቁ8 ላይ እግዚአብሄር እንደሚሰጥ የተነገረው ነገር ምንድነው? የሚሰጥበትስ ምክንያት ለምንድነው? በቁ10 ላይስ የሚሰጠው ነገር ምነድነው? ከነዚህ ሁለት ጥቅሶች በጎ ስራን በማድረግ አገልግሎት ውስጥ እግዚአብሄር ስላለው ተሳትፎ ምን እንማራለን?
7. ቁ11-12 የቆሮንቶስ ሰዎች ለሌሎች ቅዱሳን ሊያደርጉት ባለው ልግስና ውስጥ የእነጳውሎስ ተሳትፎ ምንድነው ትላለህ? የቆሮንቶስ ሰዎችና እነጳውሎስ በመተባበር ሊፈጽሙት ያለው አገልግሎት ሊያስገኝ ስለሚችለው ቢያንስ ሁለት ውጤቶች ወይም ፍሬዎች ይህ ክፍል ምን ይናገራል?
8. ቁ13-15 ሲነበብ በተለይም ቁ13 እንደ ክርስቶስ ወንጌል ተደርጎ የተነገረለት ነገር ምንድነው? በቁ8፣ በቁ14እና  በ2ኛ ቆሮ8፡1 ከምንመለከተው የልግስና አገልግሎትን አስመልክቶ ትልቅ ሥፍራ የተሰጠው ነገር ምንድነው? ማናቸውንም የልግስናን ነገር ስታደርግ ጸጋው እየረዳህ እንደሆነ ይገባሃል ወይ? ልግስና እግዚአብሄርን ከማክበር አልፎ ሌሎችንም የሚጠቅም አገልግሎት ስለሆነ እግዚአብሄር ለመለገስ የሚያስችለውን ጸጋ እንዲሰጠን ልንለምነው ይገባናል፡፡

# ጥናት አስራ ሁለት 2ኛ ቆሮ 10፡1-18

የጥናት ዓላማ፡- የቤተ ክርስትያንም ሆነ የእያንዳንዱ አማኝ ጥረት፤ ወንጌልን ያልሰሙ ወንጌልን ሰምተው እንዲድኑ የማድረግ እንጂ አምነው የዳኑትን ከአንዱ ቤተ ክርስትያን ወደ ሌላኛው ቤተ ክርስትያን ማፍለስ እንዳልሆነ ለማሳሰብ፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ስለዚህ በሌላው ሰው ክልል አስቀድሞ በተሰራ ስራ ሳንመካ፣ ከእናንተ ወዲያ ባለው አገር ወንጌልን መስበክ እንችላለን፡፡›› 2ኛ ቆሮ 10፡16

1. 2ኛ ቆሮ 10፡1-18 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-2 ላይ ጳውሎስ ራሱን በምን መንገድ ነው ሲያስተዋውቅ የምናየው? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስትያን ውስጥ ያሉትን ሰዎች ከፍሎ የሚያይባቸው ሁለት መንገዶች ምንና ምንድናቸው?
2. ቁ3-4ትን ስናነብ መንፈሳዊ ውግያ ከሥጋዊ ውግያ የሚለይባቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ይህ ክፍል ስለመንፈሳዊ የጦር መሳሪያችን ብቃትና ችሎታ ምን ይነግረናል?
3. ይህ በቁ5-6 ላይ የምናየው መንፈሳዊ የጦር መሳሪያ ሃይል እንዳለው ተነግሯል፡፡ መሳሪያችን ለማፍረስ ነው ወይስ ለመገንባት ሃይል ያለው? ለምን ይህንን ለማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡ በዚህ ክፍል መሰረት የቆሮንቶስ አማኞችን ለክርስቶስ ለመታዘዝ ካበቁ በኋላ፤ ቀጣይ ፕሮጀክት አድርገው እነነጳውሎስ የያዙት ነገር ምንድነው?
4. ጳውሎስ በቁ8 ላይ ስለራሱና ስለ አገልግሎቱ የተረዳቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ አንድ በአንድ በዝርዝር ተናገር፡፡ አንተስ ከጌታ የተቀበከከው ነገር አለህ ወይ? የተሰጠህን ስጦታ አጠቃቀምህ ጳውሎስ ከሚለው ጋራ ምን ያህል ይጣጣማል?
5. በ9-11 ላይ ሰዎች ስለእርሱና ስለአገልግሎቱ ስላላቸው አመለካከት ጳውሎስ በነዚህ ቁጥሮች ምን ይናገራል? በቁ11 ላይ ጳውሎስ ለዚህ ምላሽ አድርጎ የሚናገረውን ሃሳብ ምን ማለቱ እንደሆነ በራስህ አነጋገር አስረዳ፡፡ ከዚህ አነጋገሩ ለራሳችን ህይወት ልንጠቀም የምንችልበት ምን መመሪያ አለ?
6. ጳውሎስ በቁ12 ላይ ላለማድረግ የተቆጠበው አንድ ነገር ምንድነው? እነዚህ የጳውሎስ ከሳሾች በዚሁ ቁጥር ላይ እንደምናነበው እያደረጉ ያሉት ነገር ምንድነው? በራዕ 2፡9 እና 3፡17 ላይ የምናነባቸውን አብያተ ክርስትያናት ጳውሎስ በቁ12 ላይ የሚናገረውን እውነት የሚያረጋግጡት በምን መንገድ ነው?
7. በቁ13 ላይ ጳውሎስ ራሱንና አገልግሎቱን ከሌሎች ጋራ ከማወዳደር ይልቅ እያደረገ ያለው ነገር ምንድነው? ሥራ 22፡21 ሮሜ 11፡13 እና ገላ 2፡9ን ስታነብ የጳውሎስ የአገልግሎት መደብ ምን እንደሆነ ነው የምታየው? አንተስ የአገልግሎትህን ውጤታማነት የምትለካው ከሰዎች አገልግሎት ጋራ በማወዳደር ወይስ ለራስህ የተሰጠህን አገልግሎት በታማኝነት በማከናወንህ ነው?
8. ቁ18 ላይ የተነገረው እውነት በቁ12 ላይ ጳውሎስ ከሚናገረው እውነት ጋራ ሊሄድ የሚችልበትን መንገድ አስረዳ፡፡
9. ወደ ቁ15-16 በመመለስ በተለይም ‹‹…አስቀድሞ በተሰራ ሥራ ሳንመካ፣ ከእናንተ ወዲያ ባለው ሀገር ወንጌልን መስበክ እንችላለን›› ከሚለው የጳውሎስ አነጋገር ወንጌል ስብከትን አስመልክቶ ልንማር የምንችለው አንድ እውነት ምንድነው? በዘመኑ ያለውን አሰራር ከዚህ ጋራ በማነጻጸር ተወያዩበት፡፡ ትኩረታችን ወንጌል ያልደረሳቸው እንዲደርሳቸው እንጂ የዳኑትን ከቤተ ክርስትያን ወደ ቤተ ክርስትያን ማመላለስ እንዳይሆን ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል፡፡

# ጥናት አስራ ሶስት 2ኛ ቆሮ 11፡1-15

የጥናት ዓላማ፡- ከእነዚህ ሀሰተኛ ሀዋርያት ጋራ ማመሳሰል ባንችልም እንኳን፤ አማኞች መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው ያኖረውን ልዩ ስጦታ በማክበር በታማኝነት ለመጠቀም መትጋት እንጂ፣ ሌሎች የሚያደርጉትን በመኮረጅ እነርሱን ለመምሰል በመሞከር ጊዜያችንን ማጥፋት እንደማይገባን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እንደነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት ለመምሰል ራሳቸውን የሚለውጡ፣ ሐሰተኛ ሐዋርያትና፣ አታላይ ሰራተኞች ናቸው…ፍጻሜአቸው እንደ ሥራቸው ይሆናል፡፡›› 2ኛ ቆሮ 11፡13-15

1. 2ኛ ቆሮ 11፡1-15 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-3 ስንመለከት ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎች ለራሱ ቲፎዞነት ወይም ለራሱ ጥቅም እየኮተኮታቸው እንዳልሆነ የሚያሳየን ሃሳብ የትኛው ነው? በዚሁ ክፍል ስንመለከት የጳውሎስ ሥጋት ምን እንደሆነ ነው የምናነበው?
2. በቁ1-3 ላይ የቆሮንቶስ አማኞችን የሚያውኩትን ሰዎች በምንድነው ጳውሎስ የሚመስላቸው? ‹‹ለአንድ ባል አጭቻችኋለሁ፡፡›› ብሎ ሲናገር ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል?
3. የቆሮንቶስ ሰዎች ለክርስቶስ ካላቸው ቅንነትና ንጽህና ለማደናቀፍ እነዚህ ተንኮለኛ ሰዎች የሚጠቀሙባቸውን ቢያንስ ሶስት መሳሪያዎች ከቁ4 ላይ በመውሰድ ተናገር፡፡ አማኞች ለክርስቶስ ካላቸው ቅናትና ንጽህና ለማደናቀፍ በዚህ ዘመንስ እነዚህ መሳሪያዎች ምን ያህል በስራ ላይ ይውላሉ ብለህ ታምናለህ? አንተስ እውነተኛውን ኢየሱስ፣ ወንጌሉንና መንፈሱን ከልዩ ኢየሱስ፣ ወንጌልና ልዩ መንፈስ ለይተህ ታውቃለህ ወይ?
4. ቁ5-8 ስናነብ የጳውሎስን አገልግሎት በተለይም በቆሮንቶስ ሰዎች ፊት ከሌሎች የበታች የሆነ አገልጋይ እንደሆነ ያስቆጠረው ነገር ምን ነበር ብለህ ትገምታለህ? በነጻና ያለገንዘብ ወንጌልን ለሚያስተምር ሰው የሚኖርህ አመለካከት ከቆሮንቶስ ሰዎች የተለየ ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? በምን እንደሚለይ ተወያዩበት፡፡
5. ቁ9-10፤ 2ኛ ተሰ 3፡7-9 በአንድነት ሲነበቡ ለጳውሎስ ገንዘብ አለመቀበሉ ምክንያት ሆነው የምናያቸውን ቢያንስ ሁለት ሃሳቦች ተናገር፡፡ እነዚህ ሁለት ጥቅሶች አገልጋይ ከሚያገለግላቸው ቅዱሳን ገንዘብ መቀበል የለበትም የሚሉ እንዳልሆኑ የሚያረጋግጥል የትኛው ሃሳብ ነው? ከነዚህ ሁለት ጥቅሶች  የምትማረውን አንድ እውነት ለወገኖች አካፍል፡፡
6. ቁ11-12 እነዚህ የቆሮንቶስን ቤተ ክርስትያን የሚያውኩ ሰዎች ህይወታቸው ከ2ኛ ቆሮ 10፡17 ጋራ የሚቃረንበት ምን ነገር ታያለህ? እነዚህ ሰዎች ከእነጳውሎስ አገልግሎት ጋራ ሊወዳደሩና ራሳቸውን ከእነርሱ እኩል ለማድረግ እንዳይችሉ ጳውሎስ የሚጠቀምበት መንገድ ምንድነው?
7. በቁ13 መሰረት እንደነዚህ ያሉትን ሰዎች ጳውሎስ ምን በማለት ነው የሚጠራቸው? በቁ13-15 ውስጥ ቢያንስ ሶስት ጊዜ ተደጋግሞ የተነገረ አረፍተ ነገር ምንድነው?
8. በቁ15 ላይ ሁለት ዓይነት አገልጋዮችን እንመለከታለን፡፡ እነዚህ ሁለቱ ዓይነት አገልጋዮች ማንና ማን በማለት ነው ጳውሎስ የሚጠራቸው? የሰይጣን አገልጋዮች ዋነኛ ባህርይ ሆኖ የምታየው ነገር ምንድነው? በቅዱሳን መሃል አንዱ ሌላውን የመምሰል ጥረት ቢያደርግ ችግር ታያለህ ወይ? የሌላውን ስጦታ ለመኮረጅ ሳይሆን ‹‹በህይወታቸው ምሰሏቸው›› ምሳሌነት የተሞላ ህይወታቸውን እንድንመስል ቃሉ ያበረታታናል፡፡

# ጥናት አስራ አራት 2ኛ ቆሮ 11፡16-33

የጥናት ዓላማ፡- መከራና ስደት በግራና በቀኝ ጳውሎስን ቢያጣድፈውም እንኳን በሌሎች ቅዱሳን ህይወት የሚያልፈውን ነገር ለማየት አይኑን እንዳልጋረደው ሁሉ፣ እኛም ከምናልፍበት መከራና ችግር ባሻገር ሌሎች ቅዱሳን የሚያልፉብትን ሁኔታ ለማየት አይኖቻችንን የምንጨፍን እንዳንሆን ለማሳሰብ፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹…ተርቤአለሁ፣ ተጠምቻለሁ፣ ብዙ ጊዜ ምግብ ሳልቀምስ ኖሬአለሁ፣ በብርድና በራቁትነት ተቆራምጃለሁ፡፡ ሌላውን ነገር ሳልቆጥር፣ ዕለት ዕለት የሚያስጨንቀኝ የአብያተ ክርስትያናት ሁሉ ሃሳብ ነው፡፡ ደካማ ማነው? እኔስ አብሬ አልደከምምን? በሃጥያት የሚሰናከል ማነው? እኔስ አልቆጭምን?›› 2ኛ ቆሮ 11፡28-29

1. 2ኛ ቆሮ 11፡16-33 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ16-17 ላይ ጳውሎስ ለአንባቢዎቹ በምሳሌነት እንዳይከተሉት በማስጠንቀቂያ መልክ እየነገራቸው ያለው ሃሳብ ምን የሚል ነው?
2. ቁ20-21 የቆሮንቶስ አማኞች በሚያስገርም መንገድ እነዚህ ሰዎች እያደረጉባቸው ያሉትና ዝም ብለው በመታገስ የተቀበሉት በዚህ ክፍል የተዘረዘሩትን ቢያንስ አምስት ነገሮች ተናገር፡፡ ጳውሎስ ‹‹እኛ ግን ለዚያ እጅግ ደካሞች መሆናችንን እያፈርኩ እናገራለሁ፡፡›› ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
3. ቁ22-23 ላይ ‹‹እነሱ›› እያለ የሚጠራው እነማንን ነው? እነዚህ ሰዎች የሚመኩባቸው ነገሮች በዚህ ክፍል ምን ትመለከታለህ?
4. እነዚህ ሰዎች ከሚመኩባቸው ነገሮች መካከል ጳውሎስን እንደ እብድ ሆኖ እንዲናገር የገፋፋው አንድ ነገር ምንድነው? በቁ23 ላይ ክርስቶስን በማገልገል ‹‹እኔ እበልጣቸዋለሁ›› የሚለው አነጋገሩን ዛሬ እኛ ልንከተለው የምንችለው ጳውሎስ ያስተማረን ነገር ነው ለማለት እንችላለን ወይ? አስረዳ፡፡
5. በቁ23-27ን ስናነብ በእውነተኛ የክርስቶስ አገልጋይ ላይ ሊደርሱ ከሚችሉት ነገሮች ውስጥ ጥቂቶቹን ነገሮች በመዘርዘር ተናገር፡፡ በዚህ ዘመን ያለውን ሁኔታ ጳውሎስ ካሰፈረው ነገሮች ጋራ ስታስተያየው ምን ተመሳሳይነት ወይም ልዩነት እንደምታይ ተናገር፡፡
6. ጳውሎስ በአገልግሎቱ ያሳለፈውን መከራና ስደት ዘርዝሮ ማስፈሩ፣ የክርስቶስ አገልጋይ የሆነ ሁሉ በእነዚህ ነገሮች ሁሉ ውስጥ ማለፍ አለበት የሚል አመለካከት አለው ብለህ ታምናለህ ወይ? አስረዳ፡፡
7. በአገልግሎቱ እርሱ እንደሚበልጥ ለማስረዳት፤ ያለፈበትን መከራና ስደት ከመዘርዘር ይልቅ ሰሚዎቹን ሊማርክ የሚችልና በሰዎች ዘንድ ታላቅ ሊያሰኝ የሚችል ሌላ ምን የተለየ አቀራረብ ማቅረብ ይችል ነበረ ትላለህ? ቁ31 ላይ እግዚአብሄር ለምስክርነት የተጠራበት ምክንያት ለምንድነው?
8. ቁ28-29ን በማንበብ ጳውሎስ እውነትም ለክርስቶስ የተሰጠ አገልጋይ ነው ማለት የሚያስችለን የትኛው ሃሳብ ነው? በራስህ ላይ እየሆነ ያለው ሁኔታ አልፈህ፣ በሌሎች ቅዱሳን ህይወት የሚሆነው ነገር ያሳስብሃል ወይ? ሁልጊዜ ወየው እኔ ብሎ ስለራስ ከመቆዘም፣ ጳውሎስን በቁ29 ላይ እንደምናየው የሌሎች ድካምና የሌሎች መሰናከል የሚያስጨንቀን ሰዎች እንድንሆን ጌታ ይርዳን፡፡

# ጥናት አምስት አንድ 2ኛ ቆሮ 12፡1-21

የጥናት ዓላማ፡- ጳውሎስ በህይወቱ እግዚአብሄር በሰራው ነገር ሰዎች የእርሱን ትልቅነት ወይም ማንነት እንዳይለኩ እንደተጠነቀቀ ሁሉ፤ እኛም ከሆነው በላይ ሰዎች ከፍ አድርገው እንዳያስቡን ስለራሳችን በመናገር ራሳችንን ለመካብ መሞከር ትክክለኛ ነገር እንዳልሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ነገር ግን ማንም ስለእኔ ከሚያየውና ከሚሰማው በላይ እንዳይገምተኝ ከመመካት እቆጠባለሁ፡፡›› 2ኛ ቆሮ 12፡6

1. 2ኛ ቆሮ 12፡1-21 በአንድነት ይነበብ፡፡ በመጀመሪያዎቹ ስድስት ቁጥሮች ውስጥ ጳውሎስ መመካት ቢያስፈልግ መመካት የምችልበት ብሎ የሚያቀርበው ልምምድ ምንድነው? ይህ የተናገረው ትምክህቱ ሞኝ ሊያሰኘው የማይችለው ለምንድነው?
2. ቁ7 ላይ ጳውሎስ ያየውን የመገለጥ ዓይነት ምን በማለት ነው የሚገልጠው? በእርሱ አነጋገር፣ እግዚአብሄር ባህይወታችን ከሌሎች የበለጠ ታላላቅ ነገሮችን ሊያደርግና ሊሰራ ሲጀምር ለምንድነው ጥንቃቄ ማድረግ የሚያስፈልገን? በዚህ ቁጥር ላይ የሚታየውን የእግዚአብሄር ሥጦታ ማቴ 7፡11 ከምናነበው ሃሳብ ጋራ እንዴት ሊሄድ እንደሚችል አስረዳ፡፡
3. በቁ8-10 ላይ የእግዚአብሄርን ሥጦታ አስመልክቶ በጳውሎስና በእግዚአብሄር መሃል የሚታየው የአመለካከት ልዩነት ምንድነው? በዮሐ 14፡14 ላይ ‹‹ማንኛውንም ነገር በስሜ ብትለምኑኝ እኔ አደርገዋለሁ›› የሚለውን ጥቅስና በነዚህ ቁጥሮች ላይ የምናየውን የጳውሎስን ልመና አለመመለስ ስንመለከት፤ ሁለቱን ሃሳቦች እንዴት ማስታረቅ ይቻላል? የእግዚአብሄር ሃይል በድካምህ ሲፈጸም የተለማመዳችሁት ከወገኖች ጋራ ተከፋፈሉ፡፡
4. ቁ6 ‹‹መመካት ብፈልግ እንኳ እንደ ሞኝ መቆጠር የለብኝም›› ቁ11 ‹‹በመመካቴ ሞኝ ሆኛለሁ›› የሚሉት ሁለት አነጋገሮች የሚቃረኑ ሃሳቦች ናቸው ወይ? ካልሆነስ ምን ለማለት እንደፈለገ አስረዳ፡፡ ከቁ11 አነጋገሩ የቆሮንቶስ ሰዎች ትምክህት ውስጥ እንዳይገባ በምን መንገድ ሊረዱት ይችሉ እንደነበረ ተናገር፡፡
5. ቁ11-13ትን ስታነብ ጳውሎስ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በማወዳደር የሚናገራቸው ሁለት ዓይነት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? አወዳድሮ ሲያሳያቸው ራሱንና የቆሮንቶስ ቤተ ክርስትያንን ስለሚመለከትበት መንገድ ምን እናያለን?
6. ቁ14-15 ስናይ ጳውሎስ ራሱን ለቆሮንቶስ ክርስትያኖች በምን ምሳሌ አድርጎ ነው የሚያቀርብላቸው? እነዚህ ቁጥሮች ስንመከት ሐዋርያው ጳውሎስ ትልቅና እውነተኛ የወንጌል አገልጋይ መሆኑን በግልጽ ሊያሳዩን የሚችሉ ቢያንስ ሶስት ባህርያቶችን በማውጣት ተናገር፡፡ በተዘረዘሩት የአገልጋይ መለኪያዎች ራስህን ስትመዝን መለወጥ የሚያስፈልገው ነገር ታያለህ ወይ?
7. ከቁ16-21 አነጋገር ስትመለከት ቲቶም ሆነ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስትያን ላይ ሸክም ለመሆን አለመፈለጋቸውና ገንዘብ ላለመቀበላቸው ምክንያት አድርጎ የሚያቀርበው ነገር ምንድነው? ጳውሎስ የቆሮንቶስን ቤተ ክርስትያን ለመጎብኘት በሚያስብበት ጊዜ ውስጡን የሚያስፈሩት ነገሮች ምን ምን ነበሩ?
8. ወደላይ ተመልሰን ቁ6ትን ስናነብ ሐዋርያው መመካት የማይፈልግበት ዋነኛ ምክንያቱ ለምንድነው? ሰዎች ስላንተ ከፍ ያለ አመለካከት እንዲኖራቸው በማለት የምታደርገው ሙከራ አለወይ? እግዚአብሄር በእኛ ውስጥ የሰራቸው ድንቅ ነገሮች ቢኖሩ ለእርሱ ክብር እንዲሆኑ እንጂ ራሳችንን ከፍ ከፍ ልናደርግበት እንደሆነ ልንረዳ ያስፈልገናል፡፡

# ጥናት አስራ ስድስት 2ኛ ቆሮ 13፡1-14

የጥናት ዓላማ፡- እንደ ጴጥሮስ የሰዎችን ህይወት መነሻና መድረሻ ለማወቅ በመሞከር ጊዜያችንን ከምናጠፋ ይልቅ፤ በራሳችን ህይወት ላይ በማተኮር ኢየሱስን መከተል የተሻለ ነገር መሆኑን መረዳት እንደሚኖርብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ጥሮስም ባየው ጊዜ ጌታ ሆይ እርሱስ ብሎ? ጠየቀ፡፡ ኢየሱስም እስከመለስ ድረስ በህይወት እንዲኖር ብፈልግ እንኳን አንተ ምን ቸገረህ? አንተ ራስህ ተከተለኝ አለው፡፡›› ዮሐ 21፡21-22

1. 2ኛ ቆሮ 13፡1-14 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-4 ውስጥ ጳውሎስ በአንድ ነገር ላይ ደጋግሞ ለቆሮንቶስ አማኞች ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ ይታያል፡፡ ይህንን ማስጠንቀቂያ መስጠት ያነሳሳው ምክንያት ምን ነበረ?
2. ቁ3-4 ላይ ጳውሎስ እየተከተለ ያለው መንገድ ኢየሱስ ያለፈበትን መንገድ እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ ኢየሱስ ያለፈበት መንገድና ጳውሎስ እየተከተለ ያለውን መንገድ በምን እንደሚመሳሰል በማነጻጸር አስረዳ፡፡
3. እንደ ጳውሎስ አነጋገር ተፈትኖ ባለፈና ፈተናውን በወደቀ ሰው መካከል የሚኖረው ትልቅ ልዩነት ምንድነው? ይህንን ጳውሎስ ሚዛን አድርጎ የተጠቀመበትን ሃሳብ የሚደግፍ ሌላ የመጽሃፍ ቅዱስ ክፍል ምን ትዝ ይልሃል? በዚሁ ክፍል ውስጥ ጳውሎስ ስለራሱና ከእርሱ እያገለገሉ ስላሉት ወገኖች ተፈትኖ ማለፍንና መውደቅን አስመልክቶ የሚናገረው ነገር ምንድነው?
4. ቁ7-8 እነጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ይጸልዩበት የነበረው የጸሎት ርዕስ ምን ነበረ? ጸሎታቸው ከግል ጥቅም የመነጨ እንዳልሆነ ሊያሳዩ የተናገረው አነጋገር ምን ለማለት እንደፈለገ በራስህ ቃላት ተናገር፡፡
5. ቁ10ርን ስናነብ እነጳውሎስ ከጌታ ተቀብለናል የሚሉት ምን ነገር ታያለህ? እነጳውሎስ ከጌታ ተቀበልን የሚሉትን ነገር ሊጠቀሙ ይችላሉ የምትላቸው ስንት መንገዶችን ታያለህ? ከነዚህ መካከል እነጳውሎስ ለመጠቀም የመረጡት የትኛው መንገድ ነው ነበረ?
6. ጳውሎስ በቁ9 ላይ የተናገረው አነጋገር ከቁ10 አንጻር ሲታይ ምን ለማለት እንደፈለገና ደግሞም እነዚህ ሁለት ቁጥሮች እንዴት እንደሚያያዙ አስረዳ፡፡ አንተስ ከጌታ የተቀበልከውን ጸጋ እየተጠቀምክበት ያለኸው በምን ዓይነት ይሆን? ከጌታ የተቀበልከው ማናቸውም ስጦታ ሌሎችን ለማገልገልና ለማነጽ እንጂ ከሌሎች በላይ ሆኖ ለመታየት እንዳለሆነ ልትረዳ ያስፈልግሃል፡፡
7. ቁ11ድን ሲጀምር ማን እያለ ነው እነዚህን ሰዎች የሚጠራቸው? ስለጳውሎስ ይህንን ያህል ያልሆነ አመለካከት እያላቸውና በንቀት፣ ሥልጣኑን ለመቀበል የማይፈልጉትን ሰዎች ‹‹ወንድሞች›› እያለ መጥራቱ ምን ያስተምረናል?
8. ወደ ቁ3 ተመልሰን ስናይ፤ የቆሮንቶስ ሰዎች እየጠየቁ ያሉት ጥያቄያቸው ነበረ? በቁ5-6 ላይ ጳውሎስ የእነዚህ ሰዎች ጥያቄ ምን ሊሆን እንደሚገባው ነው የሚናገራቸው? የአንተስ ጥያቄ የራስህ ነገር ነው ወይስ የሰዎች? ኢየሱስ በዮሐ 21፡21-22 እንደሚነግረን የሰዎችን ሁኔታ ለማወቅ ጊዜህን ከማጥፋት ይልቅ የራስህን ህይወት እየመረመርክ ኢየሱስን በመከተል ላይ ማተኮር ይሻልሃል፡፡